OFFICE OF ARTS & CULTURE
CITY OF SEATTLE

# የ2024 የኪነቶች በፓርኮች ውስጥ መመሪያዎች

## *የይዘት ማውጫ (ወደዚያ ዘርፍ እንዲወስድዎት ከዚህ በታች ያለውን አማራጭ ጠቅ ያድርጉ):*


1. የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ አጠቃላይ እይታ
    a. የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ ዓላማ
    b. ብቁነት/መስፈርቶች
    c. የገንዘብ ድጋፍ
    d. የግምገማ መስፈርቶች
    e. የጊዜ መስመር
2. የማመልከቻ አጭር መግለጫ እና አካላት
3. ተመራጭ ፓርኮች


## *የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ አጠቃላይ እይታ*

የሲያትል የኪነ-ጥበብ እና የባህል ቢሮ (ARTS) በመላ ከተማው ውስጥ በሚገኙ መናፈሻዎች የኪነጥበብ እና የማህበረሰብ ዝግጅቶችን ለማሳደግ ከሲያትል ፓርኮች እና መዝናኛ ጋር በሽርክና እየሰራ ነው። በኪነቶች በፓርኮች ውስጥ ፕሮግራም (Arts in Parks program) አማካኝነት ከተማዋ በመላው ሲያትል ውስጥ ሁሉ እና በተለያዩ ማህበረሰቦች እየተካሄደ ላለው ደማቅ የባህል ስራ ላይ መዋዕለ ንዋይ ታደርጋለች።

ይህ ፕሮግራም የሰፈር ጥበባት ምክር ቤቶችን፣ ማህበረሰብን መሰረት ያደረጉ ቡድኖችን፣ እና ግለሰብ አርቲስቶችን የተመረጡ የሲያትል መናፈሻዎችን በከተማው ውስጥ ዝቅተኛ አገልግሎት በሚያገኙ እና የኢኮኖሚያዊ ችግሮች ያሉባቸውን ሰፈሮች ማንቀሳቀስ ለሚፈልጉ ይደግፋል። ይህ የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ ኪነጥበቦችን እና ባህላዊ ተሳትፎን የሚያስተዋውቁ/የሚያበረታቱ አዲስ እና በደንብ የተቋቋሙ የበዓላት አከባበሮችን ወይም ክስተቶችን፣ ብዝሃነትን የሚያከብሩትን፣ የማህበረሰብ ግንኙነቶችን የሚገነቡትን፣ እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን፣ አካል ጉዳተኝነቶች ያላቸው ሰዎችን፣ አዲስ ሰፋሪ እና ስደተኞችን፣ እንዲሁም የስደተኞች ማህበረሰቦች እና የቀለም ማህበረሰቦችን ጨምሮ በስርአታዊ ጭቆና ከተጎዱ ማህበረሰቦች ጋር በማገናኘት በኪነጥበብ እና ባህል በኩል ፓርኮችን እያነቃቃ ይደግፋል።

መረጃ፡ የፕሮግራም ሥራ አስኪያጅ፣ አሽራፍ ሃሻም ፣ን (Ashraf Hasham)፣ በ (206) 514-1057 ወይም ashraf.hasham@seattle.gov ያግኙ

TTY: 711 ወይም (800) 833-6384፣ ቴሌ-ብሬይል: (800) 833-6385።

| **ማመልከቻ**<br>ማመልከቻው በመስመር ላይ (ONLINE) ይገባል። ማመልከቻው በሲያትል ከተማ የድጋፍ ስጦታ ድህር<br>መግቢያ በኩል በFLUXX ላይ በ<br>https://seattle.fluxx.io/user_sessions/newይገኛል<br><br>የኮምፒውተር ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት መዳረሻ ከሌለዎት፣ ሰራተኞችን በተቻለ ፍጥነት ያግኙ። | **የሚከፈተው**<br>ማክሰኞ፣ መስከረም 26፤ 2023፤ 10:00 ጧት (ፓሲፊክ)<br>**የሚያበቃበት**<br>ማክሰኞ፣ ህዳር 7፣ ቀን 2023፤ 5:00 ፒኤም (ፓሲፊክ) |
|---|---|
| **የመረጃ ክፍለ-ጊዜዎች:** ስለ ፕሮግራሙ እና ምርጥ የሆነ ማመልከቻ እንዴት እንደሚያስገቡ አጠቃላይ እይታን ይቀበሉ።<br><br>**አውደ ጥናት 1**<br>ረቡዕ ጥቅምት፣ 4፤ 12:00 - 1:30 ፒኤም.<br>በመስመር ላይ / ምናባዊ<br>እዚህ ይመዝገቡ<br><br>**አውደ ጥናት 2**<br>አርብ፣ ጥቅምት 13፤ 12:00 - 1:30 ፒኤም<br>በጄፈርሰን የማህበረሰብ ማእከል በአካል<br>እዚህ ይመዝገቡ | **ካለ ቀጠሮ የሚገቡ ክፍለ-ጊዜዎች:** እነዚህ ከማመልከቻ ስርዓቱ ጋር ድጋፍ የሚያገኙበት የጥያቄ እና መልስ ክፍለ ጊዜዎች ይሆናሉ።<br><br>**ካለ ቀጠሮ የሚገባ ክፍለ ጊዜ 1**<br>ሰኞ ጥቅምት 23፤ 6:00 - 7:30 ፒኤም<br>በመስመር ላይ / ምናባዊ<br>እዚህ ይመዝገቡ<br><br>**ካለ ቀጠሮ የሚገባ ክፍለ ጊዜ 2**<br>ቅዳሜ፣ ህዳር 4፤ 10:00 ጧት - 12:00 ፒኤም.<br>በአካል በጋርፊልድ የማህበረሰብ ማእከል<br>እዚህ ይመዝገቡ |

*ለእርዳታ፣ ለመገናኘት:*

- *ማመልከቻ ወይም መዳረሻ*: አሌክስ ቼዝን (Alex Chase) በ (206) 718-3430 ወይም alexandra.chase@seattle.gov ይጠቀሙ
- *የመስመር ላይ የቴክኒክ ድጋፍ*: Sarah Blumenfeld ( sarah.blumenfeld@seattle.gov)
- **የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን ጨምሮ፣ በእርስዎ ቋንቋ ሊያናግሩዎት የሚችሉ አስተርጓሚዎች አሉን።** ብቻ ይደውሉልን እና እርስዎ የሚናገሩትን ቋንቋ ይንገሩን። አስተርጓሚ እንዲቀላቀለን ስንደውልለት ለአጭር ጊዜ ይጠብቃሉ።

## ***<u>የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ ዓላማ</u>***

የባህል እንቅስቃሴዎች እና ፓርኮች የነቃ፣ ጤናማ፣ እና ሁሉንም ማህበረሰብ የሚያሳትፉ አስፈላጊ አካላት ናቸው። ከሲያትል ፓርኮች እና መዝናኛ ጋር በመተባበር ARTS ከኪነጥበብ እና ከማህበረሰቡ ቡድኖች ጋር መተባበርን በመፈለግ ሁሉም አርቲስቶች እና ማህበረሰቦች ታሪኮቻቸውን፣ ጥበባቸውን፣ ባህሎቻቸውን፣ እና ልምዶቻቸውን

ለማካፈል እና ለማጉላት ነፃነት፣ ኤጀንሲ፣ እና መድረክ ያላትን ከተማ ለመፍጠር ይፈልጋል። ዘር፣ መደብ፣ ጾታ፣ ዕድሜ፣ ችሎታ፣ ትምህርት፣ የትውልድ አገር፣ ዜግነት፣ ሃይማኖት፣ እና ጾታዊ ዝንባሌን ሳይለይ።

## ***ብቁነት/ መስፈርቶች***

**አመልካቹ** የሚከተሉትን ማድረግ አለበት:

- አርቲስት ግለሰብ፣ የሰፈር ኪነቶች ምክር ቤት፣ ወይም የአካባቢ ማህበረሰብን መሰረት ያደረገ ቡድን መሆን
  - ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው፣ አካል ጉዳተኞች ሰዎች፣ ኤዲስ ሰፋሪ እና ስደተኛ ማህበረሰቦች፣ እና የቀለም ማህበረሰቦችን ጨምሮ እጅግ በስርአታዊ ጭቆና የተጎዱ ማህበረሰቦችን የሚወክሉ ድርጅቶች እና አርቲስት ግለሰቦች እንዲያመለክቱ ይበረታታሉ።
- የፌዴራል የታክስ መታወቂያ መለያ ቁጥር ያለው እና በሲያትል ከተማ ውስጥ የተመሰረተ መሆን።
  - የሚያመለክቱ ቡድኖች በ501(c)(3) ለትርፍ ያልተቋቋሙ መሆን አይጠበቅባቸውም ወይም የገንዘብ አያያዝ ወኪል መጠቀም አይጠበቅባቸውም።

**ፕሮጀክቱ** የሚከተሉትን ማድረግ አለበት:

- አንድ ጉልህ የሆነ የኪነ ጥበብ እና የባህል ይዘት ያለው፣
- ለህዝብ ነፃ እና ክፍት የሆነ፣
- ዋስትና/ ኢንሹራንስ ያለው፣
- ከበቂ በታች የመረጃ/ የቁሳዊ ሀብት ላላቸው አርቲስቶች እና ማህበረሰቦች መድረክ የሚሰጥ፣
- የሲያትል ፓርክ እና መዝናኛ ተልእኮ መግለጫ የሚያከብሩ (ለመጫወት፣ ለመማር፣ ለማሰላሰል፣ ማህበረሰቡን ለመገንባት፣ እና መሬቱን የመንከባከብ ኃላፊነት የተሞላበትን አገልግሎት ለማሳደግ የእንኳን ደህና መጣችሁ እና ደህንነቱ የተጠበቀ እድሎችን ለመስጠት)፣
- ከሚያዚያ 1 እስከ ህዳር 30፣ 2024 ባለው ጊዜ ውስጥ ብቁ በሆነ የሲያትል መናፈሻ ውስጥ ይካሄዳሉ።
  - በዚህ ሰነድ መጨረሻ ላይ **የተመረጡትን ፓርኮች ዝርዝር** ይመልከቱ።
  - በዳውንታውን ወይም በሲቲ ሴንተር ፓርኮች ወይም በፐሌይፊልድ እና ከማህበረሰብ ማእከላት አጠገብ ያሉ አረንጓዴ ቦታዎች ላይ የሚደረጉ ዝግጅቶች ለዚህ የገንዘብ ድጋፍ ብቁ አይደሉም። በዚህ ሰነድ መጨረሻ ላይ ***ያልተመረጡትን ፓርኮች ዝርዝር*** ይመልከቱ።

ለዚህ ፕሮግራም በዓመት አንድ (1) ማመልከቻ ብቻ ማስገባት ይችላሉ።

## ***የገንዘብ ድጋፍ***

የድጋፍ ገንዘብ የተሰጣቸው ድርጅቶች ለአንድ (1) አመት የኪነቶች በፓርኮች ውስጥ (AIP) የገንዘብ ድጋፍ (በ2023 ለሚካሄዱ ክንውኖች) ያገኛሉ:- የአርቲስት ክፍያዎች፣ የግብይት እና የማስተዋወቂያ ክፍያዎች፣ የፕሮጀክት አስተዳደር እና የሰራተኞች ወጪዎች፣ አቅርቦቶች፣ የመሳሪያ ኪራዮች ወይም ሌሎች ከምርት ጋር የተያያዙ ወጪዎች፣ አስፈላጊ ፈቃዶች፣ እና ከ 10% የማይበልጥ ከምግብ ጋር የተያያዙ ወጪዎች። የገንዘብ ድጋፎች ለገንዘብ ማሰባሰብ፣ ስጦታዎች፣ ድርጅታዊ አስተዳደራዊ ወጪዎች ከፕሮጀክቱ ወይም ከመሳሪያ ግዢ ጋር በቀጥታ ያልተገናኙ ሊውሉ ***አይችሉም***። ለዚህ ፕሮግራም ምንም ከፊል የሆነ የገንዘብ ድጋፍ የለም፣ እና በ2024 የበጀት ፍቃድ ላይ የተመሰረተ ነው። አመልካቾች ለሚከተሉት የገንዘብ ድጋፍ ደረጃዎች ማመልከት ይችላሉ:

- $1,300 ዶላር (ክስተት ማካሄዳቸው ምንም ያለፈ የተያዘ መረጃ መኖር አያስፈልግም)
- $2,600* ዶላር
- $5,200 ዶላር
- $7,800** ዶላር

**$2,600 ዶላር ደረጃ እና ከዚያ በላይ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ዝግጅቶችን የማዘጋጀት ታሪክ ያላቸው ቡድኖች ብቻ ማመልከት ይችላሉ።*

***ከዚህ ቀደም በ$7,200/$7,800 የገንዘብ ድጋፍ የተደረገላቸው ክንውኖች/ ፕሮጀክቶች ባለፉት ዓመታት በ$5,200 ወይም ከዚያ በታች የገንዘብ ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ፣ ከዝግጅቶች/ ፕሮጀክቶች ቢያንስ ለ12 ሰአታት የህዝብ ፕሮግራሞችን[1] ብቁ በሆነ መናፈሻ ቢያንስ ለ አራት(4) ቀናት[2] ማቅረብ ከሚችሉ በስተቀር። ይህ ገደብ ከማህበረሰብ በተሰጠ ግብረ-መልስ ላይ የተመሰረተ እና ተጨማሪ ፕሮጀክቶችን ለመደገፍ እና ለክስተቶች አቅምን ለማጎልበት እንዲረዳ ነው።*

## ***<u>የግምገማ መስፈርቶች</u>***

ለፕሮግራሙ የተረከቡ የሀሳብ አቅርቦቶች በሚከተሉት መስፈርቶች ይገመገማሉ (**በአጠቃላይ 50 ነጥብ**):-

- **የፕሮጀክት ጥንካሬ (20 ነጥቦች):-** የኪነቶች ተሳትፎን እና የማህበረሰብ ግንኙነቶችን ትርጉም ባለው እና ልዩ በሆኑ ልምዶች/ ገጠመኞች በኩል የሚያበረታታ ግልጽ፣ በሚገባ የታሰበበት ክስተት። ከባህላዊ ማህበረሰብ፣ ሰፈር፣ ወይም ሌሎች የፍላጎት ማህበረሰቦች ጋር ትክክለኛ ግንኙነትን ያሳያል።
- **የማህበረሰብ ተጽእኖ (20 ነጥቦች) :-** የፕሮጀክቱ እቅድ ሁሉን አቀፍ ለመሆን፣ ማህበረሰብን ያጐለብታል፣ ተሳትፎን ያበረታታል፣ ለተለያዩ ታዳሚዎችን ይደርሳል፣ ትርጉም ያላቸው ጥረቶችን ይገልጻል፣ እንዲሁም በተለይ በመዋቅራዊ ዘረኝነት እና ጭቆና እጅግ ለተጎዱት ተደራሽነትን ይፈጥራል።
- **አዋጭነት (10 ነጥብ) :-** አደራጅ ቡድን/ግለሰብ ይህንን እና/ወይም ሌላ ክስተት (ዎችን) ለማቅረብ ወይም በሌላ መልኩ ፕሮጀክቱን በተሳካ ሁኔታ የማስፈፀም አቅምን የሚያሳይ የተረጋገጠ የባለፈው የክንዋኔ መዝገብ፤ የማህበረሰብ ተሳትፎ እና ድጋፍ ማስረጃ፤ እና ለዝግጅቱ ግልጽ፣ ተጨባጭ በጀት አለው።
- ***ተመራጭ ፓርኮች:-*** በዝርዝሩ ውስጥ በተጠቀሱት በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ተመራጭ ፓርኮች ውስጥ ለሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ቅድሚያ ይሰጣል፣ ይህም በተለይ በሕዝብ ብዛት መጨመር ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

## ***<u>የጊዜ መስመር</u>***

*ይህ የጊዜ መስመር ግምታዊ ነው እና ሊለወጥ ይችላል።*

- **ህዳር 2023 መጨረሻ**:- ቀነ-ገደቡን ተከትሎ ራሱን የቻለ የአቻ ቡድን አርቲስቶች፣ የማህበረሰብ ተወካዮች፣ እና የዝግጅት አዘጋጆች በዘር ፍትሃዊነት እና በግልጽ አድልዎ ስልጠና ላይ ይሳተፋሉ።

---

[1] *ህዝባዊ ፕሮግራሚንግየሚያመለክተው ክስተትዎ ለህዝብ የሚተዋወቅበትን ሰዓት ነው (ለምሳሌ፣ በማስተዋወቂያ ማቴሪያሎች ላይ የተዘረዘሩትን ህዝቡ እንዲሳተፍባቸው ያቀዱዋቸውን እንቅስቃሴዎች)።* ይህ የክስተትዎ ወይም የእንቅስቃሴዎ መጀመሪያ ጊዜ ከመጀመሩ በፊት የማዋቀር ወይም የስልጠና ሰዓቶችን አያካትትም።

[2] የዝግጅቱ ቀናት ተከታታይ ሊሆኑ ወይም ለዚህ ፕሮግራም ብቁ በሆነው የጊዜ ገደብ በሚያዚያ እና ህዳር 2024 መካከል ሊሰራጭ ይችላል።

- **ታህሳስ 2023**፡- የእኩያ ፓነል በፕሮግራሙ ብቁነት መሰረት ማመልከቻዎችን ይገመግማል እና ይመዘግባል።
- **በጥር 2024 መጀመሪያ ላይ፡-** የእኩያ ፓነል ከፕሮግራሙ መስፈርቶች ጋር በተገናኘ እያንዳንዱን ማመልከቻ ለመወያየት እና የገንዘብ ድጋፍን በተመለከተ ሃሳብ ለመስጠት ይገናኛል።
- **በጥር 2024 መጨረሻ**፡- ከARTS፣ ከሲያትል ጥበባት ኮሚሽን፣ እና ፓርኮች እና መዝናኛ አመራር የመጨረሻ ምክሮችን ይገመግማል እና ለማጽደቅ ድምጽ ይሰጣል።
- **የካቲት 2024 መጀመሪያ ላይ፡-** አመልካቾች ለገንዘብ ፈንዲንግ የቀረቡ መሆን አለመሆናቸውን ይነገራቸዋል።
- **ሚያዚያ - ህዳር 2024**፡- አጋሮች ዝግጅቶቻቸውን ያዘጋጃሉ እና የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት የሪፖርት ሰነዶቻቸውን ያቀርባሉ።

## ***የማመልከቻ አጭር መግለጫ እና አካላት***

*የሲያትል ከተማ አዲስ የማመልከቻ ስርዓት FLUXX፣ በ2021 ውስጥ መጠቀም ጀመረች። እስካሁን ያላደረጉት ከሆነ፣ ማመልከቻውን መክፈት/ ማዳረስ ከመጀመርዎ በፊት አንድ አዲስ አጠቃላይ ገጽታን መፍጠር ያስፈልግዎታል።*

- **የግንኙነት እውቂያ/ ፊስካል ስፖንሰር ኢንፎርሜሽን:** ይህ ክፍል በመመዝገቢያው የግል መገለጫ ውስጥ አስቀድሞ ያልተጠየቀ ለዚህ ማመልከቻ የተለየ ሆኖ ነገር ግን ተጨማሪ የግንኙነት እውቂያ መረጃን ይሰጣል።
- **የስነሕዝብ መረጃ፡**ይህ እንደ ማመልከቻዎ አካል አይገመገምም፣ ይልቁንም በፕሮግራሞቻችን አማካኝነት ስለምናገለግላቸው ማህበረሰቦች የበለጠ እንድንማር ለመርዳት እና፣ ፕሮግራሞቻችንን የበለጠ ፍትሃዊ ለማድረግ መስራታችንን እንድንቀጥል ነው። *ሁሉም ጥያቄዎች በምርጫ ናቸው፣ ነገር ግን ወደ ቀሪው ማመልከቻው ከመቀጠልዎ በፊት መጠይቁ መቅረብ/ መረከብ አለበት።*
- **የማመልከቻ መረጃ:** ከፕሮጀክትዎ ጋር የተያያዙ አጭር ጥያቄዎች፣ ቀኖችን፣ አካባቢን፣ መጠን/ሚዛን ወዘተ ጨምሮ።
- **የፕሮጀክት መረጃ:** የእነዚህ ጥያቄዎች አላማ ስለ እርስዎ ክስተት/ፕሮጀክት፣ ይህ ክስተት ስለሚያገለግለው ማህበረሰብ እና ስለራስዎ ስላለፉት አንዳንድ መረጃዎችን ለማካፈል ነው።
    1. **የፕሮጀክት ርዕስ:** የክስተትዎ ስም
    2. **የፕሮጀክት አጭር መግለጫ:** የክስተትዎ ወይም የፕሮጀክትዎ አጭር መግለጫ (ለምሳሌ፣ በአንድ የማህበረሰብ የቀን መቁጠሪያ ላይ የሚያስቀምጡት ጥቂት ነገር)።
    3. **የፕሮጀክት መግለጫ:** የገንዘብ ድጋፎች እንዲደረግለት የፈለጉለትን ሥርዐተ በዓል፣ የዝግጅት፣ ወይም ፕሮጀክት እንቅስቃሴዎችን ይግለጹ። በፕሮጀክትዎ ወይም በክስተትዎ ውስጥ ኪነ ጥበብ እና ባህል እንዴት ተለይተው እንደሚታዩ መረጃን ያካትቱ።
    4. **ማህበረሰብን በኪነ-ጥበብ እና በባህል መገንባት**: እባክዎትን በዝግጅትዎ ማን እንደሚሳተፍ ይግለጹ። የእርስዎ ፕሮጀክት ማህበረሰብን ለመገንባት ኪነ-ጥበብን እና ባህልን እንዴት ይጠቀማል? አካታች ለማድረግ፣ የብዝሃን/ የተለያዩ ህዝቦችን ለማሳተፍ፣ እና ተደራሽነትን ለመጨመር ጥረቶችዎ ምን እንደሚሆኑ ይግለጹ።
    5. **ዳራ/ ያለፈ ሂደት እና አቅም**: የእርስዎን የኪነ ጥበብ ፕሮግራም ማዘጋጀትን እና የማቅረቢያ እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ አንድ አጠር ያለ ታሪክ ያቅርቡ። የክስተትዎን ስኬት እንዴት አድርገው ያረጋግጣሉ? ይህ

ፕሮጀክት ወይም ክስተት በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ የሚረዱትን ማንኛውንም ቁልፍ ሽርክናዎች (ከድርጅቶች፣ ቡድኖች፣ ወይም ግለሰቦች ጋር) ይግለጹ።

- **በጀት: የፕሮጀክቱን የበጀት አብነት** ይሙሉ እና ይስቀሉት (upload) (በኪነት በመናፈሻዎች ውስጥ (Arts in Parks) ድረ-ገጽ ላይ በ"Materials" ስር የተገናኘ)። በ2024 ውስጥ ባጀትዎ የክስተቱን ወጪ የሚያንፀባርቅ መሆን አለበት፣ ገቢ እና ወጪዎች መመዛዘን አለባቸው፣ እና ማንኛውም የተለገሱ እቃዎች ወይም አገልግሎቶች መካተት አለባቸው። እንዲሁም ስለ በጀትዎ ደግሞ አንዳንድ ማስታወሻዎችን ለማካተት የሚያስችል ቦታም አለ።

## ***ተመራጭ ፓርኮች***

**እባክዎትን የሲያትል ፓርኮች እና መዝናኛ ድህረ ገጽ ይጎብኙ እና ከዚህ በታች ስለተዘረዘሩት ፓርኮች የበለጠ መረጃ ለማየት Park Finder ን ይጠቀሙ።**

### CENTRAL

- Dr. Blanche Lavizzo Park
- Judkins Park
- Flo Ware Park
- Pratt Park
- Powell Barnett Park

### NORTH

- Albert Davis Park
- Ballard Commons Park
- Lake City Mini-Park
- Licton Springs Park
- Little Brook Park
- Sandel Park
- Virgil Flaim Park

### SOUTHEAST

- Beer Sheva Park
- John C. Little Park
- Martha Washington Park
- Othello Park
- Pritchard Island Beach

### SOUTHWEST

- Duwamish Waterway Park

- Highland Park Playground
- Myrtle Reservoir Park
- Roxhill Park
- Westcrest Park

## *ብቁ ያልሆኑ ፓርኮች*

**ዳውንታውን ወይም ሴንተር ከተማ ለኪነቶች በፓርኮች የገንዘብ ድጋፍ ፕሮጀክቶች ብቁ አይደሉም። በእነዚህ ፓርኮች ውስጥ ላሉት ፕሮጀክቶች ሌሎች የገንዘብ ምንጮች አሉ።**

- 2100 Westlake
- Alaskan Way Blvd
- Bell Street Park
- Belltown P-Patch / Belltown Cottage Park
- Cascade Playground
- City Hall Park
- Denny Regrade Park Off-Leash Area
- Donnie Chin International Children’s Park
- Elliott Bay Bike Path
- Freeway Park
- Hing Hay Park
- Kobe Terrace
- Lake Union Park
- McGraw Square
- Myrtle Edwards Park
- Occidental Square
- Pier 62/63
- Pioneer Square Park
- Plymouth Pillars Park and Off-Leash Area
- Prefontaine Place
- Tilikum Place
- Union Station Square
- Victor Steinbrueck Park
- Waterfront Park
- Washington Street Boat Landing

- Westlake Square
- Westlake Park

**የሚከተሉት የመጫወቻ ሜዳዎች፣ ፓርኮች፣ እና አረንጓዴ ቦታዎች ለኪነቶች በፓርኮች ውስጥ በገንዘብ ለሚደገፉ ፕሮጀክቶች ብቁ አይደሉም። አብዛኛዎቹ እነዚህ የመጫወቻ ሜዳዎች እና መናፈሻዎች ከማህበረሰብ ማእከላት ተጠቃሚ ይሆናሉ፣ የገንዘብ ምንጮች ያላቸው ወይም በእነዚህ ፓርኮች ውስጥ ላሉት ፕሮጀክቶች ሌሎች የድጋፍ ምንጮች አላቸው።**

- Alki Playground
- Ballard Playground
- Bitter Lake Playfield
- Camp Long
- Carkeek Park
- Delridge Playfield
- Discovery Park
- Garfield Playfield
- Green Lake Playfield
- Hiawatha Playfield
- Laurelhurst Playfield
- Loyal Heights Playfield
- Magnolia Playfield
- Magnuson Park
- Meadowbrook Playfield
- Miller Playfield
- Montlake Playfield
- Northgate Park
- Rainier Beach Playfield
- Rainier Playfield
- Ravenna-Eckstein Park
- South Park Playground
- Van Asselt Playground
- Walt Hundley Playfield
- West Queen Anne Playfield
- Yesler Terrace Park